ጋዜጠኛ ዩሀ. ተሰማ መንገሻ ፍሬው

# በሉዓላዊት አገር ሉዓላዊ ህዝብ

ዛሬ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች 'እንኩራበታለን' ለማለት የሚቃጣቸው የኢትዮጵያ ታሪክ በሃገራችን ህልውና ላይ አስለቺ በሆነ ሁኔታ እየተደጋገመ የተቃጣውን ፈተና የኢትዮጵያ ልጆች በሃገር ፍቅር እልህ እየተነሱ በመወጣት በዚቸ ምድራቸን ላይ ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ያቆዩልን አኩሪ ታሪክ ነው:: በዚህ በረዥም ጊዜ ታሪካቸን የኢትዮጵያ ህዝብ የሃገርህ ሉዓላዊነት ተደፍሯልና "ተነስ" በተባለ ቁጥር የራሱን የመብት ጉስቁልነት ጉዳይ ወደጉን እየተወ፣ የራሱን የፍትህ ጥማት በይደር እያስታገሰ ገዥዎቹን እየተከተለ በየግንባሩ ተዋድቋል:: ተሰውቷል:: ድል አድርጓል:: ግን ይህ ሁሉ ሲሆን በመስዋእትነቱ አቅፍ ደግፍ ባቆያት በዚቸ ሉዓላዊት ሃገሩ እሱ ራሱ ሉዓላዊ የሚሆንበትን ሥርዓት መገንባት እስከዛሬ አልተሳካለትም::

የዛሬ ሁለት ዓመት የሸዓቢያ መሪዎች በኃይል የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ሲደፍሩ እንደተለመደው የኢትዮጵያ ህዝብ "ተነስ" ተባለ:: ከዳር እስከዳር ተነሳ:: እንደተለመደው ይህ ነው የማይባል ፈተና ተቀበሉ፣ በደርዘን ሺ የሚቆጠሩ ልጆቹን ሰውቶ፣ የሃገሪቱን ሉዓላዊነት አስከበረ:: እንደተለመደው ገዥዎች በህዝብ ልጆች ደም የተገኘውን ድል እነሱ በህዝብ ላይ እንደተጐናጸፉት ድል ቆጠረው፣ እንደተለመደው ከቁጭን ውሃ የማይ ቆጥሩትን የህዝብ ልጆች ደም ንቀውና አዋርደው ልጆቿ ሰማእትነት ሉዓላዊነቷ በተከበረና ክብሩ በተጠበቀ ሃገራቸን ህዝብ እየተዋረደና እየተናቀ የሲኦል ኑሮ የሚቸል ትከሻ ዛሬም ያለው መስሏቸው የወያኔ መሪዎች ከባድ ስህተት በመፈጸም ላይ ይገኛሉ::

ዛሬ የሃገር ሉዓላዊነት ጥያቄ ጊዜያዊ እልባት አግኝቷል:: ነገር ግን ሃገራችን እንደዛሬ ሁለት ዓመቱ በሺህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች በየወህኒው የሚማቀቁባት ሃገር ነች:: ዛሬም እንደዛሬ ሁለት ዓመቱ በአስተዳደር ጉድለት በሚሊዩን የሚቆጠሩ ዜጐቿ በርሃብ አለንጋ የሚሰቃዩበት ሃገር ነች:: ዛሬም እንደዛሬ ሁለት ዓመቱ የወያኔ ካድሬዎች ጸረ ህዝብ አፈና፣ የግፈኛ ገዥዎች የዘፈቀደ ሥርዓት፣ ለጥቂቶች ቀጥ ያጠ መቀማጠል በዙሃኑን የኑሮ ቀስትና የነፈገ ኢፍትሃዊ ሥርዓት ተደራርበው የሚጨፍሩባት ሃገር ናት:: ባጭሩ ህዝባችን መብቱንና ሉዓላዊነቱን ለማረጋገጥ የሚያካሂደው ትግል ገና እልባት ያላገኘና ገና ብዙ ውጣ ውረድ የሚጠብቀው ግን ደግሞ በምንም ዓይነት ሳይበርድ መቀጠል፣ መቀነባበርና መፋፋም ያለበት ትግል ነው:: ቀጣዩን ትግል ለመያያዝ በምንሰናዳበት በአሁኑ ወቀት ከሸዓቢያ ወረራ ወዲህ በሃገራችን ከተከሰተው የትግል ጉዞ አንዳንድ መሠረታዊ ግንዛቤያችን መጨበጥ ያስፈልጋል::

አንደኛ:: የወያኔ መሪዎች አገኘን በሚሉት ድል ተኩራርተውና አብጠው "የአፈና አገዛዛቸንን እንደቀደሞው እንቀጥላለን" ሊሉ የሚቸሉበት ሁኔታ ውስጥ እንዳይሉ ለኛም ለነሱም ግልጽ መሆን ይኖርበታል:: ይህ በወራሪው ኃይል ላይ በኢትዮጵያ ልጆች ከባድ መስዋእትነት የተገኘው ድል በነሱም ላይ የተገኘ እንጂ የእነሱ ድል አይደለም:: ይህ ድል የወያኔ መሪዎች ሰባት ዓመት ሙሉ ደብዛው እንዲጠፋ ክፉኛ የተፈታተኑት ኢትዮጵያዊነት በነሱ ጸረ ኢትዮጵያ ራእይና ከሣራ ፖለቲካ መቃብር ላይ እንደገና መልሰ ማበብ የጀመረበት የመላ ኢትዮጵያ ልጆች የጋራ ህዝባዊ ድል ነው::

ባለፉት ዓመታት የአክሱም ጉዳይ አያገባህም ያሉት ህዝብ ባድመና ዛለአንበሳ ዛልቀ ሲሰዋ ጉጠኝነት ሞቶ መቀበሩን መገንዘብ ይኖርባቸዋል:: ባንዲራህ ብጣሸ ጨርቅ ነው ሲሉት የነበረው ዜጋ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማዩ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ህይወትን ያህል ክቡር ነገር የሚሰውለት የክብር ምልክቴ ነው እያለ ሲሰዋ ኢትዮጵያዊነት

ማለት የሚታይ፣ የሚጨበጥ የሚዳሰስ ኃያል ነገር እንደሆነ አምነው መቀበል :ህዝ አርስ በእርስ አናክሰውና አዳክመው የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም ሲያሴሩ የመላ ኢትዮጵያ ወጣቶች ከያሉበት ተሰባስበው ደማቸውን ከትግራይ ልጆች ደም እየቀላቀሉ ሲሰው አይተዋልና ይህንን የህዝቦች ወንድማማችነት የማይፍረሱ እድል ከምንጊዜውም ይልቅ የመነመነ መሆኑን የግድ መቀበል አለባቸው:: ባጭሩ በዚህ ሁሉ መስዋእትነት ለወያኔ መሪዎች የተላለፈው መልእክት "አበጃችሁ ቀጥሉ" የሚል መልእክት ሳይሆን "በቃችሁ ታረሙ" የሚል ጥሪ ነው:: የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ለተከፈለው መስዋእትነት ተገቢ ክብሩን ሰጥተው፣ ይህንን የህዝብ ፈተና ከመጤፍ ቆጥረው ይታረሙ አይታረሙ ጊዜ የሚያሳየው ጉዳይ ነው::

የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች የመረጡትን ጉዳና በመርጡም የሃገራችን ዲሞክራቶች ተግባር እጅግ ገልጸ ነው:: በኢትዮጵያ ልጆች የጋራ ትግልና መስዋእትነት ስንዋደቅለት የነበረው ኢትዮጵያዊነት መልሶ ማንሰራራት ችሏል:: ጉጠኝነትና ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ተሸንፍ የህዝቦች ወንድማማችነት እንደገና ታድሷል:: ይህንን ድል እየተንከባከብንና በሱም እየታገዝን በዚች ሉዓላዊት አገራችን ህዝባችንም ሉዓላዊነቱን ለሚያስከብርበት ሥርዓት የጀመርነውን የጋራ ትግል በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ሞራልና በአዲስ ወኔ ለመቀጠል ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ መነሳሳት ይኖርብናል::

ሁለተኛው ቁም ነገር የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች በሃገር ሉዓላዊነት ተጋድሎ ስም ህዝባችን በነሱ ላይ የሚያካሂደውን የመብት ትግል እንዲያቀዘቅዝ የቀየሱት ስትራቴጂ ሙሉ በሙሉ መክሸፉን የሚመለከት ቁም ነገር ነው:: የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፉት የፈተና ዘመናት ያደርግ እንደነበረው ሳይሆን የሻእብያን ወረራ ለመቋቋም የተንቀሳቀሰው ከወያኔ አገዛዝ ጋር የተያያዘውን የመብትና የፍትህ ፍልሚያ በይዋል ይደር አስተላልፎ አልነበረም:: የሻእብያ ወረራ በተቀሰቀሰበት ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ካለፈው ግማሽ ምእተ ዓመት ጀምሮ ለፍትህ፣ ለዲሞክራሲና ለነጻነት በገዢዎች ላይ እየተነሳ፣ አገኘ እያጣ፣ ድል አድርጎ ድል እየተነሳ ባካበተው የትግል ልምድና ብስለት እየተመረኰዘ፣ ራእዩን በሚጋሩ ታጋይ ልጆቹ እየተመራ በወያኔ ገዥዎች ላይ አፍላ ትግል ላይ ስለነበረ አገር ተወረረ ሲባል በደመነፍስ ድንበር ላይ ብቻ አነጣጥሮ አልተነሳም:: ህዝባችን በደረሰበት የፖለቲካ ብስለት ደረጃ የሃገርን ሉዓላዊነት ጥያቄ ከህዝብ ሉዓላዊነት ጉዳይ ነጥሎ ባለማየቱ "በአንድ ግንባር ከወራሪዎች በሌላ ግንባር ከግፈኛ ገዥዎች ጋር ትግል ለማካሄድ ንቃቱም፣ ፍላጐቱም ብቃቱም አለኝ" በማለት በጥንድ ግንባር ጥንድ ትግል ለማካሄድ ተነሳ:: በግንባር እየተዋደቀ ያለ ህዝብ በመሃል አገርም ለመብቱ የሚያደርገውን ተጋድሎ አፋፋመ::

በዚህ የተደናገጡት ገዥዎች "ድንበራችንን ከህዝብ ጋር ሥልጣናችንን በህዝብ ላይ" የሚል መፈክር አንግበው እነሱም ጸረ ህዝብ ትግላቸውን አፋፋሙ:: የህዝብ ልጆች በወረራው ግንባር እየተማገዱ በሚረግፉበት ወቅት እንኳን ለዚህ መስዋእትነት የሚገባውን ክብር ነፍገው ለህዝብ መብት በተንቀሳቀሱባቸው የሃገራችን ሌሎች የህዝብ ልጆች ላይ ሌላ የአመጽ ግንባር ከፈቱባቸው:: በባድመ፣ ሾራሮና ዛላአንበሳ ለወራሪዎች እብሪት በመገበር ላይ ያለው የኢትዮጵያ ልጆች ደም አይበቃ ይመስል ሌሎች የኢትዮጵያ ልጆች በህዝብ ሉዓላዊነት ግንባር በወያኔ ካድሬዎች ተረሸኑ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ታፈኑ፣ ታሰሩ:: ድሃ ገበሬዎችና ሌሎች ሠርቶ አዳሪዎች ከመሬታቸውና ከሥራ ገበታቸው እየተፈናቀሉ ጉሮሮቸው እንዲዘጋ ተበየነባቸው:: ርሃብተኞች በተቃዋሚነት እየተፈረጁ የእለት ጉርስ ተነፈጋ

ገፅ 2



ቸው:: ይህ የጸረ ህዝብ ገፍ ውርደቦች ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ሉዓላዊነትን ለማስከበር ቆርጦ ተነስቷልና ተጋድሎውን ለአንድ አፍታም አልገታውም:: እንዲያውም የወያኔ አገዛዝ ባዘጋጀው ምርጫ ተብየ ቲያትር ሳቢያ ይበልጡን እያየለና እየተፋፋመ በመምጣቱ ሃገራችን ህዝባዊ ትግልና ጸረ ህዝብ ዓመጽ ተያይዘው የሚያድጉበት የትንንቅ ወቅት ውስጥ ገባች::

ይህ ትግል የኢትዮጵያ ህዝብ በገዛ አገሩ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቱን ሙሉ በሙሉ አስከብሮ ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁሉም በተቀበላቸው መስፈርቶች መሰረት ነጻ፣ ርትዓዊና ሃቀኛ ምርጫ ለማካሄድ የተደረገ ህዝባዊ ተጋድሎ ቢሆንም የግንቦቱ ምርጫ ተብዬ ነገር በማይመስል ውጤት በወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች አሸነፍን ባይነት ተጠናቋል::

በአንጻሩ ደግሞ በምርጫው እንቅስቃሴ ወቅት የተነሳሳው ህዝባዊ ትግል በግንቦት ማግስት እንዳይከስምና እንዲያውም በይበልጥ ተቀነባብሮ እንዲቀጥል ኢተፖድህ ባደረገው ያላሰለሰ ጥረትና ድጋፍ በሃገር ውስጥ በትግሉ ወላፈን ውስጥ የሚገኙ የሃገራችን ዲሞክራቶች ስለቀጣዩ ትግልና ስለቅንብሩ ለመወያየት ሚያዝያ መጨረሻ ላይ በጠሩት አገር አቀፍ ጉባኤ ለጋራ ትግላቸው ሁኔታዎችን ለማመቻቸት አንድ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች አስተባባሪ ኮሚቴ አቋቁመዋል:: ይህ ኮሚቴ የመጀመሪያ ተግባሩ አርጐ የወሰደው የግንቦቱን ምርጫ ሂደት በሚገባ ተንትኖ ለቀጣዩ ትግል ስትራቴጂ መቀየስ እንደመሆኑ መጠን ይህ ምርጫ ተብየ ነገር ከመጀመሪያ እስከመጨረሻና ከዳር እስከዳር የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ትያትር እንጂ ከነጻና ርትአዊ ሂደት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው አጋልጦ በአንዳንድ አካባቢዎችና ወረዳዎች ብቻ ሳይሆን በሃገሪቱ በሙሉ እንዲሰረዝና ሌላ ምርጫ እንዲካሄድ ጥሪ አድርጓል:: ከዚህም በማያያዝ የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱ ተረጋግጦለት ነጻና ርትአዊ ምርጫ እስከሚካሄድ ድረስ ካለፈው ትግል ትምህርት እየቀሰመ የጋራ ትግሉን ለመቀጠል ዝግጁ መሆኑን አረጋግጧል::

ኢተፖድህ በዚህ ሂደት ውስጥ የሃገር ውስጡ ትግል እንዲጐለብት፣ የውስጡና የውጩ በይበልጥ እንዲቀነባበርና በውጭ ያሉ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ጥረታቸውን አስተባብረው የትግል ተሳትፏቸውን ከፍ እንዲያደርጉ የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ የቆረጠ መሆኑን እያረጋገጠ በመጭው ጊዜ የሃገራችን ሉዓላዊነት ሙሉ በሙሉ እየተከበረ ለህዝባችን መብት በሚካሄደው ትግል ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ሁሉ በሚቀጥሉት ነጥቦች ላይ በማተኮር ሃገራዊና ዲሞክራሲያዊ ግዴታቸውን እንዲያጡ ጥሪውን ያስተላልፋል::

1ኛ/ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ሲባል ወዉ በደርዘን ሺ የሚቆጠሩ ወጣቶች፣ መኮንኖችና ባለሌላ ማእረግ የሠራዊቱ ዓባላት በህይወታቸው ለከፈሉት መስዋእትነት ተገቢ ክብሩን መስጠት ማለት ከሁሉ አስቀድሞ እናት፣ አባትና ቀሪ ዘመድ በሙሉ በስነሥርዓት እርም ማውጣት ስለሆነ ቀደም ሲል የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማህበር ባጠየቀው መሠረት የተሰውት ዜጐች ማንነት በሚገባ ተመዝግቦ መረጃው ለዘመዶቻቸው ባስቸኳይ እንዲገለጽ

2ኛ/ ከሻዓቢያ መሪዎች ጋር ማንኛውም የሰላም ድርድር በሚደረግበት ወቅት እንዳለፉት ዘመናት በህዝብ ጀርባ በምስጢር የሚካሄዱ ውሎች ወይም ደግሞ እንደዚሁ በሚስጥር በወያኔ ኢህአዴግ መስፈርት ብቻ ዲሞክራት ከሚባሉ ሌሎች ኤርትራውያን ጋራ የሚደረጉ ምስጢራዊ ስምምነቶች የሚያመጡት መዘዝ የታየ ስለሆነ ማንኛውም ድርድር የኢትዮጵያን ክብር፣ ሰላምና ዘላቂ ጥቅም በሚያስከብር ሁኔታ እንዲካሄድ ግልጽነት እንዲኖረው

3ኛ/ በዚህ የሰላም ድርድር የእስረኞችን ልውውጥ ጉዳይ አስመልክቶ የሚደረግ ማንኛውም ውል ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በጸኑ እሥራትና የግዴታ ሥራ ካምፖች ውስጥ ታጉረው ህይወታቸውን በማክሰም ላይ የሚገኙ [illegible] ከ15ሺ በላይ የሚሆኑ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊትና የህዝብ ደህንነት አባላት እንዲሁም ሲቪል እስረኞች እንዲፈቱ [illegible] የሚለው ሃሳብ አንዱ የአጀንዳ ነጥብ ሆኖ እንዲቀርብ

ገጽ 3



4ኛ/ የጥርስ ወርቅ ሳይቀር ያለ የሌለ ንብረታቸውን እየተነጠቁ ድንበር ላይ የተወረወሩ ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ከድርድር አጀንዳዎች ውስጥ ቦታ እንዲሰጠውና ለተዘረፈ ሃብታቸው አስፈላጊው ካሣ እንዲከፈላቸው

5ኛ/ የግንቦቱ ምርጫ ከዳር እስከዳር የተጭበረበረ በመሆኑና በአንዳንድ አካባቢዎች አንዳንድ ጉድለቶች ታይተዋልና በነሱ ብቻ ይደገማል የሚለው ተራ ማጭበርበር በመሆኑ ለጥቂት መቀመጫዎች ሲባል ጥቂት ሰዎች ይህንን የመሰለ ርካሽ የከፋፍለህ ግዛ ወጥመድ ውስጥ መግባታቸው አጠቃላዩን የሽፍጥ ሂደት ቅንጣት ስለማይቀይረው የሃገሪቱ ዲሞክራቶች በሙሉ በጠየቁት መሠረት የግንቦቱ ምርጫ በሙሉ ተሰርዞ ሌላ ምርጫ እንዲዘጋጅ

6ኛ/ በምርጫው እንቅስቃሴ ሳቢያ ባለፉት ወራት ለእስር የተዳረጉ ዜጎች ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ፣ ህይወታቸው ላለፈ ዜጎች ተጠያቂ የሆኑት ካድሬዎችና የመንግሥት ባለሥልጣናት ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ ከሥራ የተባረሩ ወደ ሥራ ገበታቸው፣ ከመሬታቸው የተፈናቀሉ ወደ ማሳቸው ባስቸኳይ እንዲመለሱ

7ኛ/ ከግንቦት ምርጫ በኋላም በቅደሙት ወራት ተቃዋሚዎችን በመደገፋቸው አፋኝ ካድሬዎች ዓይን በገቡ ዜጎች ላይ የቀጠለው የማፈን፣ የማሰርና የማስፈራራት ተግባር ባስቸኳይ እንዲቆምና ከሁሉም በላይ ደግሞ በርሃብ ለተጉዱ ወገኖቻችን ከዓለም አቀፍ በጎ አድራጊዎች የተላከው ነፍስ አድን እርዳታ ያለአንዳች የፖለቲካ መስፈርትና አድልዎ ለተቸገሩት ሁሉ እንዲታደል

8ኛ/ የወላይታ ህዝብ ህልውናውን ለማረጋገጥና ህገ መንግሥታዊ መብቱን ለማስከበር ባደረገው ትግል ሳቢያ ለተፈጠረው የህይወት መጥፋት ተጠያቂዎቹ በሙሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ የታሰሩት ዜጎች ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱና ህዝቡ ላቀረበው ዲሞክራሲያዊ ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኝ

9ኛ/ የወያኔ/ኢህአዴግ አመራር በአንድ በኩል አንዳንዶቹን እያባበለ የተቃዋሚዎችን ሠፈር በመከፋፈል በሌላ በኩል ደግሞ በራሱ መስፈርት ብቻ ዲሞክራቶች ከሚላቸው የኤርትራ ድርጅቶች ጋር በህዝብ ጀርባ በመመሳጠር የሃገራችንን መሠረታዊ ችግሮች መፍታት እንደማይቻልና እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ሙከራ ሰላም መረጋጋትና ልማት እንደውሃ ለጠማቸው አገራችንና አካባቢያችን የባሰ ትርምስና ጥፋት የሚያመጣ አደገኛ ስሌት መሆኑን ተገንዝቦ የሃገራችንን ችግሮች ለመፍታት በኢትዮጵያ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች የቀረበውን የብሄራዊ ውይይት ጥሪ እንዲቀበልና ለዚህም የብሄራዊ እርቅ ሂደት በር ለመክፈት በሺ የሚቆጠሩትን የህሊናና የፖለቲካ እስረኞች ባስቸኳይ እንዲፈታ

10ኛ/ከላይ የተጠቀሱት ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ የሃገራችን ዲሞክራቶች በሃገርም ውስጥ ሆነ በውጭ የጋራ ትግል ማካሄዳቸው ምንም አማራጭ የሌለው መሆኑን ተገንዝበው በአንድ በኩል በግል ዓላማና በአጥፊ ተልእኩ ይህን የጋራ ትግል ለመከፋፈል የሚንቀሳቀሱትን ኃይሎች እያወገዙና ተስፋ እያስቆረጡ በሌላ በኩል ደግሞ ለህብረት የሚደረገውን ጥረት የማገዙ ጉዳይ ለሃገራችን ሰላም፣ ለህዝቦቿ ወንድማማችነትና ለዲሞክራሲው ትግል ከማንኛውም ዲሞክራት ዜጋ የሚጠበቅ ሃገራዊ ሃላፊነት በመሆኑ ኢትዮጵያውያን በዚህ መልክ ለጋራው ትግል በያሉበት እንዲንቀሳቀሱ ሃገራዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን::

[illegible]

የኢተፖድህ ሴክሬታርየት
ፍራንክፈርት ጀርመን
ሰኔ 26 ቀን 1992